# ያመልክቱ

## ወደ DCPS ተመራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማመልከቻ ማስገባት

የእርስዎ ወንድ ልጅ ወይም ሴት ልጅ ወደ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (DC Public Schools (DCPS)) ስድስት ተመራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ወደ አንዱ ማመልከት ይፈልጋሉን? እነዚህ ትምህርት ቤቶች ተጨማሪ መስፈርቶች እንዲሟሉ ይጠይቃሉ። በማመልከቻው ላይ የሚከተለውን መረጃ ማቅረብ ያስፈልግዎታል:-

- PARCC ውጤቶች በሂሳብ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነ ጥበብ (ELA)
- የ2016–17 ትምህርት ዘመን የመጨረሻ ሪፖርት ካርድ
- የ2017–18 ትምህርት ዘመን ወቅታዊ ሪፖርት ካርድ
- ድርሰት( በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች የሚፈልግ)፤
- አስተያየቶች (ለአንዳንድ ትምህርት ቤቶች) ለሚሰጥ አስተዳዳሪ፣ አስተማሪ፣ እና አማካሪ የኢ.ሜል አድራሻ

ከእያንዳንዱ ተመራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የምርጫ መስፈርት ጋር ራስዎትን ለማስተዋወቅ ከዚህ በታች ያለውን ቻርት እባክዎ ይመልከቱ እና አዳዲስ ተማሪዎችን የሚቀበሉ ክፍሎችን ጨምሮ ለተጨማሪ መረጃ MySchoolDC.org ላይ “አመልክት” የሚለውን ይጎብኙ።.

### ጥቆማ

ጠቃሚ ምክር:- ተማሪዎች:- የፊደላት ግድፈትን እና የቃላት ብዛትን በመጀመሪያ ለመፈተሽ እንድትችሉ ጽሑፋችሁን በ Word ሰነድ ላይ ጻፉት። አንዳንድ ትምህርት ቤቶች የቃላት እና የቁምፊ (ቁጥር፣ ምልክት፣ ፊደል) ገደብን ያስቀምጣሉ። ጽሑፋችሁን አስቀምጡት እና በመቀጠል ዝግጁ ስትሆኑ ወደ ማመልከቻው ቀድታችሁ ለጥፉት።

| | ዝቅተኛ GPA / ዝቅተኛ ውስን የፈተና አስፈላጊ ነገሮች | ድርሰት** | አንድን ተማሪ ለመቀበል የሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች፤ | የጽሁፍ ደብዳቤዎችን አስመልክቶ የሚጽፉት አስተያየቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፤የተማሪው፤ |
|---|---|---|---|---|
| **Banneker** | ዝቅተኛው 3.0 GPA<br>“በቂ”ወይም “ከሚፈለገው በላይ” ውጤት በሂሳብ እና ንባብ በማንኛውም የተወሰነ ፈተና | አዎ ያስፈልጋል፤ | የቀረቡ ማመልከቻዎችን መገምገም፤; የተማሪውን የቤተሰብ አቅም መገምገም፤ | የእንግሊዘኛ መምህር፤; የሂሳብ መምህር፤; የተማሪዎች ጉዳይ አማካሪ፤; የትምህርት ቤቱ ዋና ድሬክተር (ርእሰ)፤ |
| **CHEC** | ምንም የለም፤ | አያስፈልግም፤* | የማመልከቻ ግምገማ; ነፍስ ወከፍ ቃለ መጠይቅ | የእንግሊዘኛ መምህር፤; የሂሳብ መምህር፤; የተማሪዎች ጉዳይ አማካሪ፤ |
| **Ellington** | ምንም የለም፤ | አዎ ያስፈልጋል፤ | የቀረቡ የተማሪ ማመልከቻዎችን መገምገም፤; ማምልከቻዎቹ በአጣሪ አካል እንዲታዩ ማድረግ፤; የመግቢያ ፈተና መስጠት፤; ለተማሪው ቤተሰብ የሚደረግ ቃለ መጠይቅ፤ | የእንግሊዘኛ መምህር፤; የሂሳብ መምህር፤; የኪነጥበብ መምህር፤ |
| **McKinley** | ዝቅተኛ 2.75 GPA በ 4 ዋና ክፍሎች (እንግሊዝኛ፣ ሁሳብ፣ ሥነ ፍጥረት፣ ማህበራዊ ተማሪዎች); 3.0 ተመራጭ “በቂ” ወይም “ከሚፈለገው በላይ” ውጤት በሂሳብ እና ንባብ በማንኛውም የተወሰነ ፈተና | አዎ ያስፈልጋል፤ | የቀረቡ የተማሪ ማመልከቻዎችን መገምገም፤; በቡደን ቃለ መጠይቅ | የእንግሊዘኛ መምህር፤; የሂሳብ መምህር፤; የተማሪዎች ጉዳይ አማካሪ፤ |
| **Phelps** | ዝቅተኛ 2.4 GPA<br>“በቂ”ወይም “ከሚፈለገው በላይ” ውጤት በሂሳብ እና ንባብ በማንኛውም የተወሰነ ፈተና 95% ወይም በላይ የክፍል ተሳትፎ” | አዎ ያስፈልጋል፤ | የተማሪ ማመልከቻዎችን መገምገም፤; የተማሪ ቤተሰቦችን ለቃለመጠይቅ ማቅረብ፤ | የእንግሊዘኛ መምህር፤; የሂሳብ መምህር፤; የተማሪዎች ጉዳይ አማካሪ፤; የትምህርት ቤቱ ዋና ድሬክተር (ርእሰ)፤ |
| **School Without Walls** | በዋና ትምህርቶች ቢያንስ 3.0 GPA ማግኘት፤ | አያስፈልግም፤ | የተማሪውን ማመልከቻዎች መገምገም፤; የተማሪ የመግቢያ ፈተና መስጠት፤;የተማሪው እና የቤተሰብ ለቃለ መጠይቅ” | ምንም የለም፤ |

*የተማሪ ዝንባሌ ዳሰሳ ጥናትን ማድረግ ያስፈልጋል

** የጽሑፍ ጥያቄዎች እና መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች MySchoolDC.org ላይ ሊገኙ ይችላሉ



ጥያቄ አለዎት? የተማሪ ማመልከቻውን ለማዘጋጀት እርዳታ ያስፈልግዎታል? በ **MY SCHOOL DC** የእርዳታ መስመር በ202-888-6336 በመደወል በሚፈልጉት ዕርዳታ ቋንቋ መጠይቅ ይችላሉ፣ ወይም በኢ.ሜል info.myschooldc@dc.gov በመጠየቅ እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።

